# በኢትዮጵያ የንግድና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት የኮሚኒኬሽንና ህዝብ ግንኙነት መምሪያ የሚዘጋጅ ወርሃዊ ዲጂታል መጽሔት

**ጥቅምት/2017ዓ.ም.**

## የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት የ2017 ዓ.ም 1ኛ ሩብ ዓመት የቦርድ ስብሰባ አካሄደ።



የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት የ2017 ዓ.ም 1ኛ ሩብ ዓመት የቦርድ ስብሰባ በኢንተር ሌግዠሪ ሆቴል አካሄደ።



ቦርዱ በዚህ ስብሰባው ከዚህ በፊት የስቀመጣቸው ውሳኔዎች አፈጻጸምን የገመገመ ሲሆን ፤ የፅ/ ቤት የ2017 የ1ኛ ሩብ ዓመት እቅድ አፈጻጸምን ላይ በመወያየት ከተጨማሪ አስተያየት ጋር ያፀደቀ ሲሆን በሌሎች አጀንዳዎች ላይም ውይይት አካሂዷል።

በተያያዘም የአማራ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ፤ ለኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት እንዲሁም ለፕሬዚዳንቱ ስብስብ አባፊራ አባጆቢር ፤ ለምክር ቤት እያደረጉት ላለው ድጋፍ እና የአገራዊ ምክር ቤቱን ለውጥ እየመሩበት ላለው ስራ እውቅና ሰጥቷል።







## በቢሮዬ የኢራን እስላሚክ ሪፐብሊክ አምባሳደር ሚስተር አሊ አክበር ረዛኤል እና ቆውንሰለር ባባክ ሸርካት ጋር በሁለቱ አገራት የንግድና ኢንቨስትመንት ግንኙነት ላይ ተዎያይተናል ::







ስብስብ አባፊራ አባጆቢር -

የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ፕሬዚዳንት

## እንኳን ለ17ኛዉ ብሔራዊ የሰንደቅ ዓላማ ቀን በዓል አደረሳችሁ! አደረሰን!



ብሔራዊ የሰንደቅ ዓላማ ቀን ዜጎች በሰንደቅ ዓላማ ፊት ቆመዉ ቃለ መሐላ በመፈፀም ለሀገራቸዉ ለኢትዮጵያና ለሰንደቅ ዓላማቸው ያላቸዉን ክብርና ፍቅር ዳግም የሚገልፁበትና የሀገራቸዉን አንድነትና ሉዓላዊነት ለማስጠበቅ ቃላቸዉን የሚያድሱበት ዕለት ነዉ።

የግሉ ዘርፍ ድምጽ!

## ማዉጫ


1ኛ ሩብ ዓመት የቦርድ ስብሰባ————-1
የሚስተር አክበር ረዛኤል ከአቶ ሰብስብ ጋር—-1
የሰንደቅ ዓላማ ቀን አከባበር————————-1
የቱርክ የቢዝነስ አታሼ ከፕሬዚደንቱ ጋር——-2
ፕሬዚደንቱ ከኪሊማንጃሮ ግሎባል አማካሪ ጋር——2
የአማራ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት———3
የምክር ቤቱ ልዑክ በደቡብ አፍሪካ————————3
የኢትዮ-ደቡብ አፍሪካ የቢዝነስ ፎረም ————-3
የኢትዮ-ደቡብ አፍሪካ መግባቢያ ስምምነት——-3
አቶ ሰብስብ አባፊራ ከኢራን አምባሳደር ——-4
አቶ ሰብስብ አባፊራ ከኩባ ኤምባሲ ጋር——- -5
አቶ ሰብስብ አባፊራ የቱርክ ኤምባሲ ————6
ዶክተር ቀነኒሳ ለሚ ከህንድ ኤንባሲ ጋር-———7
ምክትል ዋና ጸሐፊ ከግብጽ ኤምባሲ ጋር———7
ዋና ጸሐፊው ከዩክሬን ኤምባሲ ጋር————---8
ዋና ጸሐፊው ከUNDP ተወካዮች ጋር———-—-9
ዋና ጸሐፊው ከAFCHAM ተወካዮች ጋር——10
ዋና ጸሐፊው ከአፍሮኮም ተወካዮች ጋር——-11
ከጂአይዜድ ተወካዮች ጋር ውይይት ——-—12
ከማሌዥያ የመግባቢያ ስምምነት————-13
የሸማ ተራ መርካቶ ቃጠሎ————————13
ከልማት አጋሮች ውይይት————————14
የኮሜሳ ካውንስል ስብሰባ————————14
የዲጂታል ስልጠና ————————————15
በኦሮሚያ ክልል ኢንተርፕራይዞች ————15
የቢዝነስ አቻ ለአቻ ውይይት————————-16
የአዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ——16
ስልጠናው በሲዳማ ክልል ————————17
አኩሪ አተር በግዮን ሆቴል————————17
ስልጠና ከአማራ ክልል ——————————18
ለዋና ጸሐፊዎች ስልጠና————————18
የመገናኛ ብዙሃን ስልጠና በአዳማ————18
የኦሮሚያ ምክር ቤት በጣሊያን ሀገር ——20
የደቡብ ምክር ቤት በኢንዶኔሽያ————-20

አድራሻ————————————————22

**በቢሮዬ የቱርክ የቢዝነስ አታሽ ሚስተር ጠሃ አልፐርን እና ልዑካን ቡድናቸው ጋር በሁለቱ አገራት የንግድ እና ኢንቨስትመንት ግንኙነት ላይ ጥሩ ዉይይት አርገናል::**



በቢሮዬ የቱርክ የቢዝነስ አታሽ ሚስተር ጠሃ አልፐርን እና ልዑካን ቡድናቸው ጋር በሁለቱ አገራት የንግድ እና ኢንቨስትመንት ግንኙነት ላይ ጥሩ ዉይይት አርገናል::

በመጪው ጊዜ በሁለቱ አገራት መሃል ያለው የንግድ እንቂስቃሴ እንዲጠናከርና በአሰራር የታዩት ቺግሮች ተፈቶ የተሻለ ዉጤት በጋራ እንደምናመጣ ጥሩ መግባባት ፈጥረናል::



የኢትዮጵያን ምርት በቢሮዋቸው እና በቤታቸው እንዲጠቀሙም በስጦታ አበርክተናል



**የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ፕሬዚደንት አቶ ሰብስብ አባፊራ ከኪሊማንጃሮ ግሎባል አማካሪ እና የስልጠናና ኢኖቬሽን ተቋም ጋር በአፍሪካ ነጻ የንግድ ቀጠና ስምምነት ትግበራ ዙሪያ ተወያዩ።**



ሁለቱ ወገኖች በሰምምነቱ ትግበራ የኢትዮጵያ ኩባንያዎች በአፍሪካ ገበያ ተጠቃሚ በሚሆኑባቸው ጉዳዮች ዙሪያ ተነጋግረዋል። በአማካሪ ተቋሙ በኩል የአፍሪካ ነጻ ንግድ ቀጠና ስምምነት ዙሪያ መምሪያ ሰነድ እያዘጋጀ ሲሆን ለዚህ ይረዳው ዘንድም ከሚመለከታቸው የመንግስትና የግሉ ዘርፍ ባለድርሻ አካላት ጋር እየተወያየ መሆኑን የተናገሩት የኪሊማንጃሮ ግሎባል አማካሪ፣ የስልጠና እና ኢኖቬሽን ተቋም ማኔጂንግ ዳይክተር ዶክተር አዲስ ካሳሁን ናቸው።

በአፍሪካ ነጻ ንግድ ቀጠና ስምምነት ትግበራ ዙሪያ የኢትዮጵያ ኩባንያዎችና ድርጅቶች ያላቸውን የግንዛቤ ደረጃ በተመለከተ በምክር ቤቱ የሚሰሩ ስራዎችን በተመለከተ ሀሳባቸውን አቅርበዋል።





በሌላ በኩል ከአገልግሎት አሰጣጥ፣ በወጣቶች እንዲሁም በአነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች አቅም ማሳደግ እንዲሁም በአፍሪካ ገበያ ተጠቃሚነት ዙሪያ በምክር ቤቱ የሚሰሩ ስራዎችን በተመለከተ አንስተዋል። የምክር ቤቱ ፕሬዚደንት አቶ ሰብስብ አባፊራ በበኩላቸው የምክር ቤቱን የሪፎርም ስራዎችና በቅርቡ እየተተገበሩ ባሉ አዳዲስ አሰራሮች እየተገኙ ያሉ ውጤቶችን አብራርተዋል።



የንግዱ ማህበረሰብ በአፍሪካ ገበያ ተጠቃሚ እንዲሆን የአቅም ግንባታ እና የግንዛቤ ፈጠራ ስራዎች እየተሰሩ መሆናቸውን የገለጹት ፕሬዚዳንቱ ለአነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞችና ወጣቶችን ትኩረት መሰጠቱን ገልጸዋል።

ከሌሎች ሀገራት ተሞክሮዎችን በመውሰድ በምክር ቤቱ በኩል እመርታዊ ለውጥ እና ውጤት ለማምጣት እየተሰራ መሆኑንና ነጋዴው በነጻነት እንዲሰራና ተደማጭነት እንዲኖረው ለማድረግም ጥረት እየተደረገ መሆኑን አንስተዋል።

ምክር ቤቱ ዓለም አቀፍ ተቋም ነው ያሉት አቶ ሰብስብ ለኢትዮጵያ ኢኮኖሚያዊ ለውጥ እና የኢትዮጵያ ምርትና አገልግሎቶች ገበያ እንዲያገኙ ከኢትዮጵያ ኤምባሲዎች ጋርም በቅርበት እየተሰራ ስለመሆኑ ጠቁመዋል።

**የአማራ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ፤ የዳረክተሮች ቦርድ በተከበሩ የኢትዮጵያ ንግድና ዘርፍ ምህበራት ምክር ቤት እና የአማራ በሔራዊ ክልላዊ መንግስት የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት የቦርድ አባል በሆኑት በአቶ እስማኤል የተላከልኝን ታሪካዊ የተባለ ስጦታን ተቀብያለው** ምክንያቱም



የኦሮሚያ ምክር ቤትን እና አገራዊ ምክር ቤቱን በማስተባበር ለክልሉ ምክር ቤት ላደረከው አስተዋፅኦ የተበረከተ ይላል እኔም የተደረገልኝን ሺልማት በሁለቱ ምክር ቤቶች እና በራሴ ስም የላቀ ምስጋናየን አቃርባለው።



**ሰብስብ አባፊራ- የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ፕሬዚደንት**

**የአትዮጵያና ደቡብ አፍርካ ቢዝነስ ፎረም ላይ ለመገኘት የኢትዮጵያ ልዑካን ቡድንን መርቼ ደቡብ አፍሪካ ፤ ጁአንስበርግ**




**ገብቻለው** ጉዞው የአፍርካ ኩራት በሆነው አየር መንገዳችን ነበር። ጁአንስበግ የሚገኘው ኢምባስያችን ደማቅ አቃባበል እና መስተንግዶ አድርጎልናል። እኔም በልዑካን ቡድኑ ስም ከፍ ያለ ምስጋናየን አቀርባለው።



የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ፕሬዚዳንት ሰብስብ አባፊራ አባጆቢር

**የኢትዮ-ደቡብ አፍሪካ የቢዝነስ ፎረም** ( Ethio-South Africa Business Forum) በዛሬው ዕለት ተጀምረዋል ፤ በሁለቱ አገራት መካከል ያለው የንግድ እና ኢንቨስትመንት ግንኙነት የበለጠ በሚጠናከርባቸው እንዲሁም በቀጣይ በትብብር ሊሰሩ በሚችሉባቸው ጉዳዮች ዙሪያ ሰፊ ውይይት አካሂደናል ።







**የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ፕሬዚደንት ሰብስብ አባፊራ አባጆቢር**

የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ከደቡብ አፍርካው የንግድ ምክር ቤት MSME CHAMBER ጋር **የመግባቢያ ስምምነት ተፈራረመ።** በኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት በኩል ስምምነቱን የፈረሙት የምክር ቤቱ ፕሬዝዳንት ስብሰብ አባፊራ አባጆቢር እና ዋና ጸሐፉ ዶክተር ቀነኒሳ ለሚ ናቸዉ። ስምምነቱ ሁለቱ ተቋማት ንግድና ኢንቨስትመንትን በማስፋፋት ረገድ በጋራ መስራት የሚያስችላቸው ነው።







**የኢትዮጵያ ንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ፕሬዚዳንት አቶ ሰብስብ አባፊራ በኢትዮጵያ የኢራን አምባሳደር ክቡር አሊ አክባር ረዛኢን በጽህፈት ቤታቸው ተቀብለው አነጋግረዋል።**

በስብሰባው የምክር ቤቱ ዋና ጸሃፊ ዶክተር ቀነኒሳ ለሚ እና የኢራን ኤምባሲ የመጀመሪያ አማካሪ ሚስተር ኣብ ሸካት ኣረድቢሊ ተገኝተዋል።



በኢትዮጵያ እና በኢራን መካከል ያለውን የቆየ የባህል፣ፖለቲካዊ እና ማህበራዊ ትስስር በማሳደግ ኢኮኖሚያዊ ትብብርን በማጎልበት ላይ ያተኮረ ውይይት ተደርጓል።

ፕሬዚደንቱ አቶ ሰብስብ ኢኮኖሚውን ለላቀ የግሉ ዘርፍ ተሳትፎ እና ለውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት ክፍት ለማድረግ በተደረጉ ተከታታይ ማሻሻያዎች በመካሄድ ላይ ያለችውን የኢኮኖሚ ለውጥ አጉልተዋል።



በማእድን፣ በግንባታ ቴክኖሎጂ እና በማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ በትብብር ሊሰራባቸው የሚችሉ የኢኮኖሚ መስኮች መሆናቸውንም አንስተዋል። እነዚህ ዘርፎች የኢትዮጵያን የዘላቂ ልማት እና የኢንዱስትሪ ልማት ግቦች ጋር በማጣጣም የኢራን እውቀትና ኢንቨስትመንት ትርጉም ያለው ሚና እንዲጫወት የሚያስችል መድረክ እንደሚፈጥር ተናግረዋል።

ኢራን ለኢትዮጵያ እድገት ጠቃሚ የሆኑ በተለያዩ የኢኮኖሚ ዘርፎች ከፍተኛ እውቀትና ልምድ እንዳላት አፅንኦት ሰጥተው



ተናግረዋል።

አምባሳደሩ ምክር ቤቱ እና የኢራን የንግድ ምክር ቤት አጋርነታቸውን መደበኛ ለማድረግና ትብብርና ኢንቨስትመንትን ለማሳደግ የመግባቢያ ስምምነት (MoU) መፈራረም አስፈላጊ ስለመሆኑም ጠቁመዋል።



ኢትዮጵያን የሚጎበኝ የልኡካን ቡድን እንደሚኖር የገለጹት አምባሳደሩ የልዑካን ቡድኑ የኢትዮጵያን ምቹ የንግድ አካባቢ እና እምቅ የኢንቨስትመንት አማራጮችን ይለያል ብለዋል።

ፕሬዚደንቱ አቶ ሰብስብም ለዚህ ተነሳሽነት ያላቸውን ድጋፍ ገልፀው የኢትዮጵያ ኢንዱስትሪዎች ከኢራን የኢንዱስትሪ ቴክኖሎጂና ከፍተኛ እውቀት ማግኘት በሚያስችልባቸው ዘርፎች ተጠቃሚ መሆናቸውንም ጠቁመዋል።

የምክር ቤቱ ዋና ጸሃፊ ዶ/ር ቀነኒሳ ለሚ የኢትዮጵያን በርካታ የንግድ እና የኢንቨስትመንት እድሎች በማጉላት እንደ ኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን እና የሀገሪቱን የኢንዱስትሪ ፓርኮች ትስስር የመሳሰሉ ቁልፍ ተቋማትም አስፈላጊውን ድጋፍ እንደሚያደርጉ አንስተዋል።

እነዚህ ተቋማት የኢራን ባለሃብቶች በኢትዮጵያ ለመሰማራት እና ለማደግ ምቹ ሁኔታን በመፍጠር እርዳታ እና ድጋፍ ለማድረግ መዘጋጀታቸውን ዶ/ር ቀነኒሳ ተናግረዋል።

አምባሳደር ረዛኢ በኢራን ይፋዊ የስራ ጉብኝት ለማድረግ ለአቶ ሰብሲብ እና ለዶክተር ቀነኒሳ ግብዣ አቅርበዋል። ይህ ጉብኝት የመግባቢያ ሰነዱን በማጠናቀቅ እና የኢራንን የኢንዱስትሪ እና የማኑፋክቸሪንግ ዘርፎች በማየት የኢትዮጵያ ተወካዮች የኢራንን ኢኮኖሚያዊ ሞዴል እና አዳዲስ አሠራሮችን እንዲገነዘቡ ያስችላቸዋል ተብሏል።

ይህ በምክር ቤቱ እና በኢራን ኤምባሲ መካከል ያለው ትብብር ሁለቱንም ሀገራት ሊጠቅም እና የኢትዮጵያ እና የኢራን የንግድ ማህበረሰቦችን ሊያጠናክር የሚችል ጠንካራ የኢኮኖሚ አጋርነት ላይ ትልቅ እርምጃ ነው ።

**የኢትዮጵያ ንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ፕሬዝደንት አቶ ሰብስብ አባፊራ በኢትዮጵያ እና በኩባ መካከል ያለው የኢንቨስትመንት ግንኙነት ለማሳደግ በሚልባቸው እድሎች ዙሪያ በኢትዮጵያ የኩባ ኤምባሲ ሶስተኛ ፀሃፊ ናታሊስ ዲኑዝ ዩትሪያን አነጋግረዋል።**

ሁለቱ ወገኖች የኢኮኖሚ፣ የንግድና ኢንቨስትመን እንቅስቃሴን ለማሳደግ በሚያስችሉ ጉዳዮች ዙሪያ ተወያይተዋል።አቶ ሰብስብ የሁለቱን ሀገራት



የረጅም ጊዜ ታሪካዊ ግንኙነት በማጉላት ኢኮኖሚያዊ አጋርነትን ማሳደግ በሚቻልባቸው ጉዳዮች ዙሪያ ነው የተወያዩት።"በኢትዮጵያ እና በኩባ መካከል ያለው ታሪካዊ ግንኙነት ጥልቅ እና ጠንካራ ነው። ይህን ትስስር በተለይም በኢኮኖሚ ትብብር፣ ንግድ እና ኢንቨስትመንት ላይ አጠናክረን መቀጠል አለብን ብለዋል።

ናታሊስ ዲኑዝ ዩትሪያ ኩባ በንግድ እና ኢንቨስትመን የጠበቀ ግንኙነት ለመፍጠር ቁርጠኛ መሆኗን ገልጸዋል።በመጪው 40ኛው የሃቫና ዓለም አቀፍ የንግድ ትርዒት (FIHAV 2024) በኩባ ሲካሄድ የኢትዮጵያ የምክር ቤቱ ተወካዮችን ጨምሮ የልዑካን ቡድን እንዲገኝ መደበኛ ግብዣ አቅርባለች። ዝግጅቱ የኢትዮጵያን ምርቶች ለማሳየት፣ የገበያ እድሎችን ለመፈተሽ እና ከኩባ እና አለም አቀፍ ቢዝነሶች ጋር ጠቃሚ አጋርነት ለመፍጠር የሚያስችል ልዩ መድረክ ይሆናል ተብሏል።



ኢትዮጵያ በ FIHAV 2024 ተሳትፎዋ የንግድ ግንኙነቷን ለማስፋት እና አዲስ ኢንቨስትመንት ለመሳብ ያለውን ጠቀሜታ በማጉላት ግብዣውን በአክብሮት ተቀብለውታል። ኢትዮጵያ ከኩባ ቢዝነሶች ጋር በጋራ በሚጠቅሙ ዘርፎች ለመሰማራት ፍላጎት እንዳላት ለወ/ሮ



ዩትሪያ አረጋግጠዋል።

ዋና ጸሃፊ ዶ/ር ቀነኒሳ ለሚም በስብሰባው ላይ ተገኝተው በማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ በትብብር ለመስራት ያለውን አቅም አብራርተዋል።በሁለቱ ሀገራት መካከል የኢንዱስትሪ ልማትና የቴክኖሎጂ ልውውጥን ለማሳደግ በጋራ የሚደረገውን ጥረት አስፈላጊነትም አመልክተዋል። ሁለቱም ወገኖች ለብልጽግና አጋርነት ያላቸውን ተስፋ በመግለጽ ኢትዮጵያንና ኩባን የኢኮኖሚያዊ ትስስር የበለጠ ለማጠናከር ያላቸውን ቁርጠኝነት አረጋግጠዋል።

**የኢትዮጵያ ንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት እና የቱርክ ኤምባሲ የኢትዮ-ቱርክ የንግድና ኢንቨስትመንት ትስስሮችን ማጠናከር ላይ ተወያይተዋል።**



ይህ በከፍተኛ ኃላፊዎች ደረጃ የተደረገ የሙለቱ ወገኖች ውይይት በኢትዮጵያና ቱርክ መካከል ያለውን የቆየ የንግድና ኢንቨስትመንት ግንኙነት ለማጠናከር ያለመ ነው።

ውይይቱን የምክር ቤቱ ፕሬዝዳንት አቶ ሰብስብ አባፊራ የመሩት ሲሆን እና በኢትዮጵያ የቱርክ ኤምባሲ የንግድ አማካሪ ሚስተር ታሃ አልፔሬን ሳላር እና ዋና ፀሐፊ ዶ/ር ቀነኒሳ ለሚ ተገኝተዋል።



የውይይቱ ዋና አላማ በሁለቱ ሀገራት መካከል ያለውን የንግድና ኢንቨስትመንት ማሳደግ የሚቻልበትን መንገድ መፈተሽ ነው።

በውይይቱ ወቅት አቶ ሰብስብ በኢትዮጵያና በቱርክ መካከል ያለውን የንግድና ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት ታሪክ በማንሳት በጨርቃጨርቅ፣ በቆዳና ቆዳ ውጤቶች፣ በግብርና እና በአግሮ ፕሮሰሲንግ በመሳሰሉት ቁልፍ ዘርፎች መስፋፋት ያለውን አቅም አጽንኦት ሰጥተው አንስተዋል።

እያደገ ያለው የኢትዮጵያ ገበያ ለቱርክ ባለሀብቶች በርካታ እድሎችን እንደሚፈጥር፣ በተለይም ሀገሪቱ ለአፍሪካ የኢንዱስትሪ ልማት ማዕከል ሆና መቀጠሏን ጠቁመዋል። ዋና ጸሃፊ ዶ/ር ቀነኒሳ ለሚ ኢትዮጵያ በተለያዩ ዘርፎች የቱርክ ኢንቨስትመንቶችን ለመቀበል ዝግጁ መሆኗን አጽንኦት ሰጥተዋል።



ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የመንግስት ማሻሻያዎች የፋይናንሺያል ሴክተሩን ነፃ ማድረግን ጨምሮ ለውጭ ባለሃብቶች ምቹ ሁኔታ መፈጠሩን አብራርተዋል። "የኢትዮጵያ በሮች ከመቼውም ጊዜ በበለጠ ክፍት ናቸው" ያሉት ዶ/ር ቀነኒሳ ቱርክ በኢትዮጵያ የኢኮኖሚ እድገትና ኢንዱስትሪያላይዜሽን ስትራቴጂ ቁልፍ አጋር ተደርጋ ትታያለች ብለዋል።

የቱርክ የንግድ አማካሪ ሚስተር ሳላር በበኩላቸው በሁለቱ ሀገራት መካከል ያለውን የንግድ ግንኙነት አወንታዊ መሆኑን ገልጸው ቱርክ ከኢትዮጵያ ጋር ያላትን የንግድና የኢንቨስትመንት ግንኙነት የበለጠ ለማጠናከር በተለይም በኢትዮጵያ ገበያ እያደጉ ካሉ እድሎች አንፃር ከፍተኛ ፍላጎት እንዳላት ተናግረዋል።



አንዳንድ ማነቆዎች በተለይም የገቢና ወጪ ንግድ ደንቦችና ሎጂስቲክስ ጉዳዮች የንግድ ግንኙነቱን ሙሉ አቅም እያደናቀፉ መሆናቸውን ተናግረው እነዚህን ተግዳሮቶች ለመፍታት የተቀናጀ ርብርብ እንዲደረግ ጥሪ አቅርበዋል።

አቶ ሰብስብ እና ዶ/ር ቀነኒሳ ለቱርክ አቻዎቻቸውምክር ቤቱ ከኢትዮጵያ መንግስት እና የግሉ ሴክተር ወካይ እንደመሆኑ በትብብር ለመስራት ቁርጠኛ መሆኑን አረጋግጠው የንግድ እንቅፋቶችን ለመፍታት እንደሚሰራም ገልጸውላቸዋል።

ጠንካራ አጋርነት ለመፍጠር የቱርክ ኩባንያዎችን ጨምሮ ዋና ዋና ባለድርሻ አካላትን ፣የኢትዮጵያ መንግስት ተወካዮች እና የግሉ ዘርፍ ተወካዮች የሚሳተፉበት ልዩ መድረክ ለማዘጋጀት መታቀዱንም አስታውቀዋል።

ሁለቱም ወገኖች በኢትዮ-ቱርክ የንግድ ግንኙነት ላይ ያላቸውን ሰፊ እድል ገልጸው በሚቀጥሉት ወራት ተጨማሪ የትብብር ዕድሎችን ለማቻቸት ቁርጠኛ መሆናቸውን ገልጸዋል። ውይይቱም ኢትዮጵያ ከቱርክ ጋር ያላትን ኢኮኖሚያዊ ግንኙነት ወደ ተሻለ ደረጃ ለማሳደግ እና የቱርክን እውቀትና ኢንቨስትመንት በመጠቀም የጋራ እድገትን ለማምጣት ወሳኝ እርምጃ ነው።ውይይቱ የሁለትዮሽ ትብብርን ለማጠናከር እንደ የንግድ ትርኢቶች እና የአቻ ለአቻ (B2B) ውይይቶችን ማዘጋጀት እንደሚገባ በመግለጽ ተጠናቋል።

**የኢትዮጵያ ንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ምክትል ዋና ጸሃፊ አቶ ውቤ መንግስቱ በኢትዮጵያ የግብፅ ኤምባሲ ጋር በሁለትዮሽ የኢኮኖሚ ጉዳዮች ዙሪያ ተወያዩ።**



ዶ/ር ኖሃ ሻታይያ፣ የግብፅ ኤምባሲ ኢኮኖሚያዊ እና ንግድ ጽህፈት ሚኒስትር እና በአፍሪካ ህብረት ቋሚ መልዕክተኛ፣ የኢትዮጵያ ኩባንያዎች እና የግብፅ አቻዎቻቸው ጠንካራ የንግድ ትስስር ሊኖራቸው እንደሚገባ ተናግረዋል።

የግብፅ ኩባንያዎች የጋራ ዕድገትን ለማስፈንና የሁለቱን ሀገራት የንግድና ኢንቨስትመንት ለማሻሻል ከኢትዮጵያ ኩባንያዎች ጋር ተቀራርበው መስራት እንዳለባቸውም ገልጸዋል። ምክትል ዋና ጸሃፊው አቶ ውቤ መንግስቱ ለግብፅ ኩባንያዎች በኢትዮጵያ ስላለው የንግድና የኢንቨስትመንት እድል ገልጸዋል።





ሁለቱ ወገኖች የወደፊት ትብብር፣ አጋርነት፣ የንግድ ተሳትፎ እና የሁለቱም ሀገራት የኢንቨስትመንት እድሎች ላይ ተወያይተዋል።በውይይቱም የምክር ቤቱ የንግድ ፋሲሊቴሽን ክፍል ኃላፊ መታሰቢያ ጢሞቲዎስ ተገኝተዋል።

**የኢትዮጵያ ንግድና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት እና የህንድ ኤምባሲ የሁለትዮሽ የንግድ ግንኙነቶችን እንደሚያጠናክሩ ገለጹ።**

የኢትዮጵያ ንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት እና በኢትዮጵያ የሕንድ ኤምባሲ የሁለቱን አገሮች የንግድ ግንኙነት ወደ ላቀ ደረጃ ለማድረስ ያላቸውን ቁርጠኝነት አረጋግጠዋል።



ውይይቶቹ አሁን ያለውን የመግባቢያ ስምምነት (MoU) በማጠናከር እና ኢኮኖሚያዊ ትብብርን በማሳደግ ዙሪያ ያተኮሩ ናቸው። የምክር ቤቱ ዋና ፀሃፊ ዶ/ር ቀነኒሳ ለሚ ምክር ቤቱን በኢኮኖሚ ልማት ውስጥ ያለውን ወሳኝ ሚና በማጉላት በነዚህ ጥረቶች ውስጥ የአባል ምክር ቤቶች ንቁ ተሳትፎ አጽንኦት ሰጥተዋል።



የህንድ ኤምባሲ ሁለተኛ ጸሃፊ (ንግድ) ራቪ ሻንካር ኢትዮጵያ ወደ ህንድ የምትልካቸውን ምርቶች ለማስተዋወቅ ኤምባሲው እያደረገ ያለውን ጥረት አብራርተዋል።

ሁለቱም ወገኖች በኢትዮጵያ እና ህንድ መካከል ያለውን ጠንካራ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ግንኙነት እና የሁለትዮሽ ትብብርን ወደ ላቀ ደረጃ ለማድረስ በማቀድ አዳዲስ የንግድ እና የኢንቨስትመንት እድሎችን ለማስፋት እነዚህን ግንኙነቶች ማጠናከር አስፈላጊ መሆኑን አጽንኦት ሰጥተው ተወያይተዋል።

**የኢትዮጵያ ንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት በአዲስ አበባ ከሚገኘው የዩክሬን ኤምባሲ ጋር የሁለቱን አገሮች የንግድና ኢንቨስትመንት ግንኙነት ወደ ላቀ ደረጃ ለማድረስ በሚችሉ ጉዳዮች ላይ ተወያይቷል።**





የምክር ቤቱ ዋና ጸሃፊ ዶ/ር ቀነኒሳ ለሚ፥ በኢትዮጵያ ያለውን ከፍተኛ የኢንቨስትመንት እድሎች በተለይም እየተካሄደ ካለው የኢኮኖሚ ማሻሻያ አንፃር አመልክተዋል። እነዚህ ማሻሻያዎች የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንትን ወደ ኢትዮጵያ እየሳቡ ያሉበትን ሁኔታ አብራርተዋል።

በስብሰባው ትኩረት ካደረጉት ቁልፍ ጉዳዮች አንዱ ዲጂታላይዜሽን ሲሆን ዶ/ር ቀነኒሳ ዩክሬን በዲጂታል ዘርፍ ያላትን ጥንካሬ አድንቀው በኢትዮጵያ



የግሉ ዘርፍ ውስጥ ዲጂታል ለውጥ ለማምጣት ምክር ቤታቸው ከዩክሬን ጋር አጋርነት ለመፍጠር ያለውን ፍላጎት ገልጸዋል።

ትብብርን እና ቅልጥፍናን ለመጨመር ዲጂታል መሳሪያዎችን በመጠቀም ሁሉንም አባላቱን በአጠቃላይ የግንኙነት መድረክ ማቀናጀት ከምክር ቤቱ ዋና ዋና ጉዳዮች ውስጥ አንዱ መሆኑን አብራርተዋል። አክለውም ምክር ቤቱ የዲጂታላይዜሽን ፕሮጄክቱን በአጭር ጊዜ ውስጥ በዝርዝር በማቅረብ ከዩክሬን አቻዎች ጋር የበለጠ ግንኙነት ለመፍጠር ያስችላል ብለዋል።

በኢትዮጵያ የዩክሬን ኤምባሲ አማካሪ ሚስተር ማይካሂሎ ትሊያሼንኮ የምክር ቤቱ ዲጂታላይዜሽን ውጥኖችን ተገንዝበው በኢትዮጵያ እና በዩክሬን መካከል ያለውን የረጅም ጊዜ ዲፕሎማሲያዊ እና የንግድ ግንኙነት ማጠናከር ይገባል ብለዋል።ሁለቱ ሀገራት በዲጂታላይዜሽን እና በኢኮኖሚ ልማት ላይ የተሻሻሉ የትብብር ስራዎችን ሊጠቀሙ እንደሚችሉ ጠቁመዋል።

**የኢትዮጵያ ንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ዋና ጸሃፊ የሆኑትን ቀነኒሳ ለሚ (ዶ/ር) የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የልማት ፕሮግራም/UNDP ቡድንን በጽህፈት ቤታቸው ተቀብለው አነጋግረዋል።**



በሚቀጥሉት አራት ዓመታት ከመንግስትና ከሌሎች የልማት አጋሮች ጋር በጥምረት ለሚካሄደው ፕሮጀክት የትብብር እና የትብብር አሰራር በሁለቱም ወገኖች ውይይት ተደርጎበታል። ምክር ቤቱም በጁላይ 2025 ወደ ትግበራ የሚገባው ፕሮጀክት አካል መሆን ይጠበቅበታል ተብሏል።

ከምክቤቱ የልማት አጋሮች አንዱ የሆነው UNDP ቻምበር አካዳሚ ልማት አዋጭነት ጥናትን፣ የፖሊሲ አድቮኬሲ እና ሌሎችም ጉዳዮች ድጋፍ ስለማድረጉ ተነስቷል።በUNDP ከፍተኛ አማካሪ ሁዋን ሉዊስ ላራቡሬ እንዳሉት የመንግስት የግሉ ሴክተር መሪነት ደጋፊ አቋም ስራዎች ላይ ትብብርን ይጠይቃል።



የፖሊሲ ማሻሻያዎች እና የፖሊሲ ንግግሮች ጠቃሚ መሆናቸውን እና ምክር ቤቱ ከእነዚህ ጥረቶች ግንባር ቀደም እና አንዱ ተዋናይ መሆን እንዳለበት አስረድተዋል። የኢምክር ቤቱ ዋና ጸሃፊ ቀነኒሳ ለሚ (ዶ/ር) በበኩላቸው የንግድ ምክር ቤቱን ዋና ዋና አላማዎች እና ማሻሻያዎችን ያብራሩ ሲሆን እነዚህም በዲጂታይዜሽን፣ ቢዝነስ ለሰላም እና SME የአቅም ግንባታ ላይ በማተኮር ጠንካራ ሀገራዊ ቻምበር እንዲሆን ምቹ የንግድ ሁኔታን ለመፍጠር እየተሰራ ስላመሆኑም አብራርተዋል።



ምክር ቤቱ ከመንግስት እና ከለጋሽ አጋሮች ጋር በመተባበር ለመስራት ዝግጁመሆኑን የጠቀሱት ዋና ጸሐፊው ሁለቱ ወገኖች በተለያዩ መስኮች በጋራ ለመስራት መስማማታቸውንም ገልጸዋል።

**የኢትዮጵያ ንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ዋና ጸሐፊ ዶ/ር ቀነኒሳ ለሚ ከቻይና የአፍሪካ ንግድ ምክር ቤት (AFCHAM) የልዑካን ቡድን ጋር ውይይት አደረጉ።**



የልዑካን ቡድኑን የተመራው በቻይና የአፍሪካ ንግድ ምክር ቤት (AFCHAM) ስራ አስኪያጅ ዶክተር ጂልስ ጆን ሲሆን ከተለያዩ የቻይና ኩባንያዎች የተውጣጡ ተወካዮችን ያካተተ ነው። የስብሰባው ቀዳሚ ትኩረት በሚቀጥለው አመት በአዲስ አበባ ሊካሄድ የታቀደው የአለም አቀፍ የኢንቨስትመንት ፎረም ነበር።



የAFCHAM ልዑካን የመድረኩን ስኬት ለማረጋገጥ የቴክኒክ ድጋፍ ጠይቆ ከምክር ቤቱ ጋር በቅርበት ለመስራት ፍላጎት እንዳለው ገልጿል። ልዑኩ ዝግጅቱን ፍሬያማ እና ውጤታማ ለማድረግ ያለውን ፍላጎት ሲገልጽ ዶ/ር ቀነኒሳ በሰጡት ምላሽ የምክር ቤቱን ስትራቴጂክ ዓላማዎችን በማጉላት ዝግጅቱን ለማሳካት እንደሚሰሩ ገልጸዋል።



የቴክኒክ ድጋፍ ለማድረግ ተስማምተው ፎረሙ በኢትዮጵያ ቅድሚያ በሚሰጣቸው ጉዳዮች ማለትም በግብርና፣ በማዕድን እና በኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ፣ በቱሪዝም እና በማኑፋክቸሪንግ እና በሌሎችም ላይ ትኩረት ሰጥቶ መስራት እንዳለበት አሳስበዋል። የፎረሙን አጀንዳዎች ለኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ልማት ወሳኝ ከሆኑ ዘርፎች ጋር ማጣጣም አስፈላጊ መሆኑን አስምረውበታል።

በውይይቱ ላይ ከዶ/ር ቀነኒሳ በተጨማሪ ሌሎች የኢምክር ቤቱ የስራ ኃላፊዎች ተገኝተው ሀሳባቸውን በመስጠት እና ንግድ ምክር ቤቱ ኢትዮጵያ በአለም አቀፍ የንግድና የኢንቨስትመንት አማራጮች ላይ ያላትን ተሳትፎ ለማጠናከር ያለውን ቁርጠኝነት አረጋግጠዋል።

በምክር ቤቱ እና AFCHAM መካከል ያለው ትብብር የተጠናከረ ኢኮኖሚያዊ ትስስር ለመፍጠር እና ኢትዮጵያን የኢንቨስትመንት ዋና መዳረሻ ለማድረግ እንደሚያግዝም ተጠቁሟል።

**የኢትዮጵያ ንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ዋና ፀሃፊ ቀነኒሳ ለሚ (ዶ/ር) ከሩሲያ የአፍሪካ ሀገራት የኢኮኖሚ ትብብር አስተባባሪ ኮሚቴ (አፍሮኮም) ቡድን ጋር ተወያይተዋል።**

ከህዳር 12 – 14 ቀን 2024 የኢትዮጵያ – ሩሲያ ኩባንያዎች ቢዝነስ ፎረም በሚሊኒየም አዳራሽ እንደሚካሄድ በተገለጸበት ውይይት





ሁለቱ ወገኖች በኢትዮጵያና በሩሲያ መካከል ያለውን የንግድ ትብብር ማሻሻል በሚቻልበት ሁኔታ ላይ ተነጋግረዋል።

የአፍሮኮም ሊቀመንበር ኢጎር ሞሮዞቭ ወደ ሃምሳ ስድስት የሚጠጉ ትላልቅ የሩሲያ ኩባንያዎች የኢንቨስትመንት ተስፋዎችን ለመገምገም እና ከኢትዮጵያ ቢዝነሶች ጋር በተለያዩ ዘርፎች ትብብር እንደሚያደርጉ አረጋግጠዋል።



ሚስተር ኢጎር እንዳሉት ከተለያዩ ዘርፎች ማለትም ማዕድን፣ ኮንስትራክሽን፣ ትራንስፖርት፣ የሳይበር ደህንነት፣ ቱሪዝም፣ አይሲቲ እና ትምህርት የተውጣጡ ቢዝነሶች በፎረሙ ላይ እንደሚገኙ እና ከኢትዮጵያ ኩባንያዎች ጋር የንግድ-ቢዝነስ ውይይቶችን ያደርጋሉ።

ዶ/ር ቀነኒሳ ለሚ በበኩላቸው ኢትዮጵያ ሰፊ የኢንቨስትመንት እና የገበያ እድሎች እንዳላት እንዲሁም ኩባንያዎች በሁለቱ ሀገራት መካከል ያለውን የንግድ እድል እንዲፈትሹ እድል እንደሚሰጥ አብራርተዋል። እንደ ዶክተር ቀነኒሳ ገለጻ፣ ምክር ቤቱ በኢትዮጵያ ኢንቨስት ለሚያደርጉ የሩሲያ ቢዝነሶች አስፈላጊውን ድጋፍ ያደርጋል ብለዋል።



በሁለቱ ሀገራት መካከል የንግድ እና የኢንቨስትመንት ልውውጥ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ ሲሆን በውይይቱ ላይም የኢትዮጵያ የአፍሮኮም ተወካይ አቶ ተዋህደ በላቸው እና የምክር ቤቱ ምክትል ዋና ጸሃፊ አቶ ውቤ መንግስቱ ተገኝተዋል።

**የኢትዮጵያ ንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ከጂአይዜድ ተወካዮች ጋር በቅርቡ በዘላቂ የሥልጠናና ትምህርት መርሃ ግብር (STEP) ወቅታዊና የወደፊት ምዕራፎች ላይ ውጤታማ ውይይት አድርጓል።**



የፕሮጀክቱ ሦስተኛው ምዕራፍ STEP III የስልጠና ፕሮግራሞችን ከኢንዱስትሪ ፍላጎትና ከገበያ ፍላጎት ጋር በማጣጣም የኢትዮጵያን የቴክኒክና ሙያ ስልጠና ሥርዓት ማሻሻል ላይ ያተኮረ ሲሆን የተመራቂዎችን የሥራ ዕድል በማሳደግ ላይም ነው።

የምክር ቤቱ ምክትል ፕሬዝዳንት ዶ/ር አይናለም አባይነህ እና ዋና ፀሀፊ ዶክተር ቀነኒሳ ለሚን ጨምሮ ሌሎች አባላትን ጨምሮ በጂአይዜድ የኢትዮጵያ እና ጅቡቲ የኮሚሽኑ ስራ አስኪያጅ እና የፕሮግራም ኃላፊ በሆኑት በአቶ መሀመድ አሊ ካሀን የተመራውን



የጂአይዜድ ልዑክ አቀባበል አድርገውላቸዋል።

ውይይቶቹ በመካሄድ ላይ ባለው የደረጃ ሶስት ፕሮጀክት ስኬቶች ላይ ያተኮሩ ሲሆን ለቀጣይ ደረጃ IV ፕሮጀክት መሰረት የሚጥሉ ናቸው።

ደረጃ IV በኢትዮጵያ የግሉ ሴክተሩን በንቃት የሚሳተፍ የትምህርት ትምህርት በመቅረጽ የቴክክና ሙያ ስርዓት መገንባቱን ለማስቀጠል ያለመ ሲሆን በዚህም የሙያ ምሩቃን ለስራ ገበያ ጠቃሚ ክህሎት እንዲኖራቸው ማድረግ ነው።ሁለቱም ወገኖች የየቴክክና ሙያ ስርዓትን ለማሻሻል እና



ለኢትዮጵያ የኢንዱስትሪ እድገት እና የስራ እድል ፈጠራ ጥረቶች ከፍተኛ አስተዋፅኦ ለማድረግ በትብብር ለመስራት ያላቸውን ቁርጠኝነት አረጋግጠዋል።

በGIZ እና በምክር ቤቱ መካከል ያለው ትብብር ኢትዮጵያ የዓለምን ነባራዊ ሁኔታ የተረዳ ቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስርዓት ለመዘርጋት እንደሚያግዝ ይታመናል።

ትብብሩ በታዳጊ አገሮች ውስጥ የሙያ ሥልጠና ሥርዓቶችን ለመደገፍ ከጂአይዜድ ሰፊ ዓለማዎች ጋር የሚጣጣም የሥራ ዕድሎችን ለመፍጠር እና ለሀገር ውሰጥ የገበያ ፍላጎቶች ምላሽ ለመስጠት የሚያግዝ እንደሆነም ተጠቁሟል።

## ከማሌዥያ ብሔራዊ የንግድና ኢንዱስትሪ ምክር ቤት ጋር የመግባቢያ ስምምነት ተፈራርመናል

አገራዊው ምክር ቤታችን፤ የአገራዊ ኢኮኖሚ ዲፕሎማስዉን የቀጠለ ሲሆን፤ ከማሌዥያ ብሔራዊ የንግድና ኢንዱስትሪ ምክር ቤት ጋር የመግባቢያ ስምምነት ተፈራርመናል ። በኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት በኩል









ስምምነቱን የፈረሙት የምክር ቤቱ ምክትል ፕሬዝዳንት ዶክተር አይናለም አባይነህ ሲሆኑ ስምምነቱ በሁለቱ ምክር ቤቶች እና አገራት መካከል ንግድና ኢንቨስትመንትን በማስፋፋት ረገድ በጋራ መስራት የሚያስችለን ነው። ሰብስብ አባፊር አባጆቢር የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ፕሬዚደንት

**በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ሸማ ተራ ነባር የገበያ ማዕከልና በአካባቢው ባጋጠመ የእሳት አደጋ ንብረታቸው የወደመባቸውን ወንድም**



**እህቶቼን ከከተማው የስራ ኃላፊዎች ጋር በመሆን ዛሬ ጎብኝቻለው።**

**አደጋው በጣም አሳዛኝ ነው ። መርካቶ የመላው ኢትዮጵያ ልብ ናት።**





**እኔም በመላው የኢትዮጵያ የንግድ ማኅበረሰብ ስም ከጎናቸው እንደምንቆም ፤ መልሰንም እንደምናደራጃቸው ቃል ገብቻለው። በዚህ አጋጣሚም፤ እሳቱን ለማጥፋት እና ተጨማሪ ወንጀል እንዳይከሰት ለተረባረቡና የህይወት እና የአካል ዋጋ እየከፈሉ ላሉ የፖሊስ እና ሌሎች የፀጥታ አካላት፤ የእሳት አደጋ ሰራተኞች እንዲሁም ለአዲስ አበባ ወጣቶች የላቀ ምስጋናዬን አቀርባለው::**

**የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ፕሬዚዳንት ስብስብ አባፊራ አባጆቢር**

በቢሮዬ የኩባ ቢዝነስ አታሼ የሆኑት ናታልይስ ድንዛን እና የስራ ባልደረባቸዉን ተቀብዬ በሁለቱ አገራት መካከል ስላለው ንግድ እና ኢንቨስትመንት





ላይ ዉጤታማ ምክክር አርገናል ::

**ስብስብ አባፊራ አባጆቢር -የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ፕሬዚዳንት**

**17ኛው የምስራቅና ደቡብ አፍሪካ ሀገራት የጋራ ገበያ (ኮሜሳ) ቢዝነስ ካውንስል ፎረም ተካሂዷል።**

17ኛው የምስራቅና ደቡብ አፍሪካ ሀገራት የጋራ ገበያ (ኮሜሳ) ቢዝነስ ካውንስል ፎረም ተካሂዷል። 17ኛው የኮሜሳ ቢዝነስ ፎረም ጥቅምት 17/2017 ዓ.ም በቡሩንዲ ርዕሰ መዲና ቡጁምቡራ የተካሄደ ሲሆን በግብርና፣ ቱሪዝምና ማዕድን ላይ ያተኮረ ነው። በፎረሙ በቡሩንዲ ጠቅላይ ሚኒስትር ጋርቬስ ነዲርአኮቡቻ እና የኮሜሳ ሴክሬታሪያት ዋና ፀሐፊ እና የቢዝነስ ካውንስሉ ፕሬዚዳንት የተገኙ ሲሆን የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ምክትል ዋና ጸሐፊ አቶ ውቤ መንግስቱም ተገኝተዋል።




**የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ከዓለም አቀፍ የልማት አጋሮች ጋር በጋራ በሚሰሩ ስራዎች ዙሪያ ተወያየ።**






ምክር ቤቱ የግሉን ዘርፍ የኢኮኖሚ የመሪነት ሚና ለመወጣትና በመንግስትና በግሉ ሴክተር መካከል እንደ ድልድይ በመሆን የሚሰራ ሲሆን ለዚህ ደግሞ ከዓለም አቀፍ የልማት አጋሮች ጋር የተለያዩ ፕሮጀክቶችን ቀርጾ ይሰራል።



ስለሆነም ምክር ቤቱ የሚሰራቸውን ስራዎች የበለጠ ለማጠናከርና ለንግዱ ማህበረሰብ ምቹ የቢዝነስ ከባቢ እንዲፈጠር ለማስቻል የልማት አጋሮች ትብብር ወሳኝ ሚና ያለው በመሆኑ ነው ውይይቱ የተዘጋጀው።

በኢሊሊ ሆቴል በተካሄደው ፕሮግራም ላይ የተገኙት የምክር ቤቱ የስራ አመራር ቦርድ አባል ኢንጂነር አለማየሁ ንጋቱ ምክር ቤቱ ለሚሰራቸው ስራዎች የሚደረጉ ድጋፎች የሚበረታቱ እና ውጤታማ እንደነበሩ አንስተው ተጠናክረው መቀጠል እንዳለባቸው አንስተዋል።





የምክር ቤቱን ያለፉትን ዓመታት ጉዞ እና ዓላማዎች ያቀረቡት የምክር ቤቱ ዋና ጸሐፊ ዶክተር ቀነኒሳ ለሚ በተለያዩ ፕሮጀክቶች በተሰሩ ስራዎች ውጤቶች መገኘታቸውን ጠቅሰው አሁን ምክር ቤቱ በሪፎርም ላይ መሆኑንና በተለያዩ ዘርፎች ፕሮጀክቶችን ቀርጾ እየሰራ ስለመሆኑም አብራርተዋል።

ከ77 ዓመታት በላይ ያስቆጠረው እና በአፍሪካ በቀዳሚነት የሚጠቀሰው ምክር ቤቱ ለአጠቃላይ የንግዱ ማህበረሰብ ድምጽ በመሆን የተሻለ ቢዝነስ እንዲሰራና ለኢኮኖሚ እድገቱ የላቀ አስተዋጽኦ እንዲያበረክት ለማድረግ እየሰራ ስለመሆኑም በመድረኩ አቅርበዋል።

የአፍሪካ ኢኮኖሚክ ኮሚሽን፣ ጂ አይ ዜድ እና ጃይካን ጨምሮ የተለያዩ ዓለም አቀፍ የልማት አጋር ድርጅቶች በተሳተፉበት ውይይት ድርጅቶቹ አሁንም ያላቸውን ትብብር እንደሚያጠናክሩ አንስተዋል።








**የኢትዮጵያ የንግድና የዘርፍ ማህራት ምክር ቤት ከGIZ-SEQUA በተገኘ የገንዘብ ድጋፍ ከተለያዩ የክልልና የከተማ የንግድና የዘር ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤቶች ለተውጣጡ ዋና ጸሃፊዎች የዲጂታል ስልጠና እየሰጠ ነው።**





የኢትዮጵያ የንግድና የዘርፍ ማህራት ምክር ቤት ከGIZ-SEQUA በተገኘ የገንዘብ ድጋፍ ከተለያዩ የክልልና የከተማ የንግድና የዘር ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤቶች ለተውጣጡ ዋና ጸሃፊዎች የዲጂታል ስልጠና እየሰጠ ነው።

የስልጠናውን መጀመር አስመልክቶ ንግግር ያደረጉት የምክር ቤቱ ዋና ጸኀፊ ዶክተር ቀነኒሳ ለሚ የስልጠናውን ፋይዳ ገልጸው ፤ በተለይም የዲጂታል ኦላይን አገልግሎት አጠቃቀም ግንዛቤን ማሳደግእንደ ሀገር የግሉን ዘርፍ መረጃ ለማደራጀት፣ የመረጃ አያያዝን ለማዘመን ያግዛል፣ ይህም ወቅቱ የሚጠይቀውን የዲጅታል ቴክኖሎጅ በመጠቀምና በመተግበር ስራ ለመስራት አስተዋጸው ጉልህ ነው ብለዋል።

አያይዘውም ይህ የዋና ጸኃፊዎች ስልጠና ምክር ቤቶችን የሚመሩ ኃላፊዎች የሚሰጥ በመሆኑ የግሉን ዘርፍ ለመደገፍና ለማዘመን እንዲሁም ዓለማቀፍ ተወዳዳሪነት ያለው ምክር ቤት ለመገንባት የምናደርገው ጥረት ለማሳካት ትልቅ አበርክቶ ያለው ስልጠና መሆኑን ጠቅሰው ምክር ቤቱ ከተሰጡት ተልዕኮ አንዱ የአባል ምክር ቤቶችን አቅም ለማጎላበትና ለማሳደግ የተለያዩ ስልጠናዎ እየተሰጡ ነው፣ የምርምርና አድቮኬሲ የንግድና የኢንቨስትመንት ስራዎችንም ለማሳለጥ እየሰራን ነው ሲሉ ገልጸዋል።

የዲጂታል ስልጠናው በምክር ቤቱ የICT ዲቪዥን ኃላፊ ሀርያ ወልደ ገብርኤል እና የICT ባለሞያ በሆኑት አቶ ኤርሚያስ አባይ በምክር ቤቱ የቢዚነስ አመራር አካዳሚ እየተሠጠ ነው።

ዶ/ር ቀነኒሳ GIZ-SEQUA ለምክር ቤቱ እያደረገ ስላለው ድጋፍም አመስግነዋል። በስልጠናው የምክር ቤቱ ዋና ፀሐፊ ዶ/ር ቀነኒሳ ለሚን ጨምሮ ምክትል ዋና ጸኃፊው አቶ ጸደቀ ድጋፌ ተገኝተዋል።





**የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት በኦሮሚያ ክልል ለሚገኙ አነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች በአፍሪካ ነጻ የንግድ ቀጣና** ስምምነት እንዲሁም በካፒታል ገበያ እና ተያያዥ ጉዳዮች ዙሪያ ስልጠና ሰጥቷል።

ምክር ቤቱ በዋናነት ንግድና ኢንቨስትመንት እንዲስፋፋ፣ የአቅም ግንባታ እንዲሁም የምርምርና አድቮኬሲ ስራዎችን እየሰራ ሲሆን ስልጠናውም የዚሁ አካል መሆኑ ተጠቁሟል።

ከጥቅምት 12 እስከ 13/2017 ዓ.ም “Africa continental free trade agreement (AfCFTA), Capital market, Association governance, business management and Promotional skill” በሚሉ ርዕሰ ጉዳዮች በአዳማ ከተማ በተሰጠው ስልጠና ላይ ንግግር ያደረጉት የምክር ቤቱ ምክትል ዋና ጸሐፊ አቶ ጸደቀ ድጋፌ ስልጠናው ኢንተርፕራይዞቹ በአፍሪካ ገበያ የሚኖራቸውን እድል ለማስፋት እና ተጠቃሚ የሚሆኑባቸውን መንገዶች ለማወቅ እንዲሁም በማህበራት አስተዳደርና በቢዝነስ ማኔጅመንት ዙሪያ አቅማቸውን እንዲያሳድጉ እንደሚያደርጋቸው አስታውቀዋል።

ተቋማት በካፒታል ገበያ አሰራር ተጠቃሚ የሚሆኑባቸውን መንገዶች ለመረዳት እንዲሁም ምርትና አገልግሎትን ለማስተዋወቅና ስኬታማ ለመሆን መሰል ስልጠናዎች ትልቅ ሚና ያላቸው በመሆናቸው በምክር ቤቱ በኩል ትኩረት የሚሰጣቸው መሆናቸውንም አቶ ጸደቀ ገልጸዋል። ስልጠናዉ የተሰጠዉ ስልጠናው በኢትዮጵያ ንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክርቤት አስተባባሪነት በጀርመኑ የተራድኦ ተቋም GIZ -SRVC ፕሮጀክት በተገኘ ድጋፍ ነው።





**አኩሪ አተርን እሴት በመጨመር ወደ ገበያ የሚያቀርቡ ድርጅቶችና የማሽነሪ አቅራቢዎች የቢዝነስ የአቻ ለአቻ (Business to Business) የውይይት መድረክ በአዳማ ከተማ ተካሄደ።**

የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት በGIZ- SRVC ፕሮጀክት ድጋፍ ያዘጋጀው ይህ የቢዝነስ የአቻ ለአቻ (Business to Business) ውይይት በተለይም በአኩሪ አተር ላይ እሴት በመጨመር ወደ ገበያ የሚያቀርቡ አካላት ማሽነሪዎችን ከሚያቀርቡ አካላት ጋር ነው ውይይት ያደረጉት።



የምክር ቤቱ ምክትል ዋና ጸሐፊ አቶ ውቤ መንግሥቱ አኩሪ አተር ትኩረት የተሠጠው የግብርና ምርት ሲሆን በምክር ቤቱ በኩል በዘርፉ ለተሠማሩ አካላት ሥልጠናዎችን በመሥጠት ምርቱ ላይ እሴት ጨምሮ ወደ ገበያ በማቅረብና የሥራ እድል በመፍጠር ትልቅ አስተዋጽኦ እንደሚያበረክት ገልጸዋል።

ከማሽነሪ አቅራቢዎች ጋር በቅርበት በመሥራትም ዘርፉን ወደ ተሻለ ደረጃ ማሣደግ ያሥፈልጋልም ነው ያሉት። የውይይቱ ተሣታፊዎች በአዳማ ሳይንሥና ቴክኖሎጅ ዩኒቨርስቲ ጉብኝት ያደረጉ ሲሆን የዩኒቨርስቲው ቴክኖሎጅ ክፍልም ለአኩሪ አተር ማቀነባበርና እሴት መጨመር አስፈላጊ ማሽነሪዎችን መሥራት እንደሚቻል አስታውቋል።

የዩኒቨርስቲው የሜካኒካል ኢንጅነሪንግ ዲፓርትመንት ኃላፊ ዶክተር ስንታየሁ ለገሰ በዩኒቨርስቲው በኩል በቀጣይነት የተሻሉ ቴክኖሎጅዎችን መሥራት እንደሚቻል ገልጸው በአኩሪ አተር ማቀነባበርና እሴት መጨመር በተመለከተ ዘመናዊ መሳሪያዎችን በተጠቃሚዎች ጥያቄና ፍላጎት መሰረት መስራትአ ንደሚል ተናግረዋል። በሜካኒካልና ቴክኒካል ሥራዎች በቂ ባለሙያዎች እና የማምረት አቅም አለን ያሉት ኃላፊው ለማምረትና ለመሥራት እንደሚቻል ገልጸዋል። በሌላም በኩል የማሽነሪ አምራችና አቅራቢዎች በአኩሪ አተር ብቻ ሣይሆን እንደ ጤፍና በቆሎ ያሉ ምርቶችን የማቀነባበር ሥራዎችን የሚሠሩ መሣሪያዎችን አቅርበዋል።



በዝግጅቱ ላይ የአኩሪ አተር ምርትን ከእርሻ ማሣ ላይ ሣይባክን በቀላሉ መውቃት የሚችል ማሽን እየገጣጠሙና እያቀረቡ መሆናቸውን የተናገሩት የኤልያስ ጀነራል ኢንጅነሪንግ ዋና ስራ አስኪያጅ አቶ ኤልያስ በቀለ ምርትን ማምረት ብቻ ሣይሆን በተሥማሚ ሁኔታ ማከማቸት የሚችሉ በርካታ ምቹ መሣሪያዎች እንደሚያመርቱም ተናግረዋል።

የማሙሽ ጀነራል ማሽነሪ ዋና ስራ አስኪያጅ አቶ ጥላሁን ፈንታሁን በበኩላቸው የተለያዩ የግብርና ማሽነሪዎችን በመሥራትና በማቅረብ ላይ መሆኑን ገልጸዋል። ሥለሆነም በማሽነሪ አቅራቢዎችና በተጠቃሚዎች መካከል ተቀራርቦ መሥራት እንደሚገባና የእሴት መጨመር ሥራውም ተመጋጋቢ መሆን እንዳለበት በአጽንኦት ነው የተናገሩት።

በአኩሪ አተር ምርት ሂደት የማምረት እንዲሁም የእሴት መጨመርና ለገበያ ለማቅረብ እንደ ማሽግ ያሉ ተያያዥ ሥራዎችም ትኩረት ሊሠጣቸው እንደሚገባ ተነሥቷል።

**አዳማ ሣይንሥና ቴክኖሎጅ ዩኒቨርሠቲ በምርት ማቀነባበር ላይ ለሚሠሩ አምራቾች ማሽነሪዎችን ለማምረት ዝግጁ መሆኑን ገለጸ።**

የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት በአኩሪ አተር ምርት እሴት መጨመርና ለገበያ ማቅረብ እንዲቻል በኦሮሚያ እና በሲዳማ ክልሎች የሚገኙ አኩሪ አተርርን ወደ ተለያዩ የምግብ አይነቶች በማምረት ለገበያ የሚያቀርቡ ተቋማትና የምርት ማቀነባበሪያ ማሽነሪ አምራቾች በአዳማ ከተማ ባካሄዱት የቢዝነስ የአቻ ለአቻ (Business to Business) የውይይት መድረክ ተሣታፊዎች በዩኒቨርሠቲው ጉብኝት አድርገዋል።



የዩኒቨርሠቲው የኢንጅነሪንግ ትምህርት ክፍል ኃላፊ ዶክተር ስንታየሁ ለገሰ በአሁኑ ወቅት ዩኒቨርሠቲው በአኩሪ አተር እና ሌሊችንም ምርተች ከማምረት ጀምሮ የሚያገለግሉ ማሽነሪወችን ማምረት እንደሚችል ገልጸዋል።



ምርት ከማምረት፣ እሴት ከመጨመርና ወደ ምግብነት መቀየር ብቻ ሣይሆን የምግቡን የንጥረ ነገር ይዘት የማስተካከል ሥራዎችን እንደሚሠሩም ነው አቶ ስንታየሁ የተናገሩት። በዩኒቨርሠቲው ጉብኝት ያደረጉት ተሣታፊዎችም አኩሪ አተርን ለአጠቃቀም ቀላል ከማድረግ፣ ከመከካት፣ ከማጠብ፣ ከመፍጨትና ከሌሎችም ጉዳዮች ጋር የተገናኙ ጥያቄዎችን አቅርበው በትምህርት ክፍሉ ምመህራን ምላሽ ተሠጥቶባቸል።


በመሆኑም ተጠቃሚዎ ፍላጎታቸውንና የሚፈልጉትን የማሽነሪ አይነትና ዲዛይን በማቅረብ በዩኒቨርሠቲው በኩል መሠራት እንደሚችል ተነሥቷል። የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤትም ድርጅቶቹን በመደገፍ በተለይም በማምረቻ ኢንዱሥትሪው በኩል የተሻለ ሥራ ለመሥራት ጥረት እያደረገ መሆኑን ገልጿል።

**የአኩሪ አተር ምርት ላይ እሴት በመጨመር የተለያዩ ምግቦችን ለማዘጋጀት የሚያስችል ተግባራዊ ስልጠና በአዲስ አበባ ከተማ በግዮን ሆቴል ሲሰጥ ቆይቶ ተጠናቀቀ ።**

የአኩሪ አተር ምርት ላይ እሴት በመጨመር የተለያዩ ምግቦችን ለማዘጋጀት የሚያስችል ተግባራዊ ስልጠና በአዲስ አበባ ከተማ በግዮን ሆቴል ሲሰጥ ቆይቶ ተጠናቀቀ ።



የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ከGIZ SRVC ፕሮጀክት በተገኘ የገንዘብ ድጋፍ ከአማራ ክልል የተለያዩ ዞኖችና ወረዳዎች ለተውጣጡ ሰልጣኞች ከአኩሪ አተር ምርት ከ15 በላይ የተለያዩ ምግቦችን በማዘጋጀት ስራ ለመጀመር የሚያስችል የክህሎት ስልጠና ለሶስት ተከታታይ ቀናት ሲሰጥ ቆይቶ ተጠናቀቀ።



ክፍል ታላፊ ዶ/ር ሙሉጌታ ክንዱ እንደገለጹት ወደ ቢዝነስ በመቀየር የራሳችሁን ገቢ ማሳደግ፣ የስራ በማነቃቃት የሀገራችን የኢኮኖሚ እድገት ላይ

የስልጠናው ማጠቃለያ ላይ ተግኝተው ንግግር ያደረጉት የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት የእቅድ ዝግጅትና የፕሮጀክት ማኔጅመንትና ሀብት ማፈላለግ የስራ ሰልጣኞት ያገኛችሁትን የተግባር ላይ ስልጠና እድል መፍጠርና የአካባቢያችሁን ኢኮኖሚ የራሳችሁን አሻራ ማሳረፍ ይገባል ብለዋል።



አያይዘውም ለስራ የሚያስፈልጉ ግብኣቶችን በራሳችሁ አቅም ለማሟላት ጥረት ማድረግ እንዳለባቸው አሳስበው የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤትም የገበያ አማራጭ በመፍጠርና ገበያ በማፈላለግ እንዲሁም ምርቶቻቸውን በማስተዋወቅ በኩል ከሚመለከታቸው አጋር አካላት ጋር በጋራ በመስራት በኩል ድጋፍ እንደማይለያቸው ገልጸዋል።



ሰልጣኞችም ስራ ለመጀመር የሚያስችላቸውን ግብአቶች በየከተሞቻቸው ካሉ የመንግስት አካላትና ከከተማና ክልል ቻምበር ተቋማት ጋር በጋራ በመስራትና ጥያቄኣቸውን እያቀረቡ ያሉባቸሁን ክፍተቶች በመሙላት አቅማችሁን በማሳደግ ተወዳዳሪ መሆን እንዳለባቸው አሳስበዋለው። ለሶስተኛ ዙር በአዲስ አበባ ጊዮን ሆቴል የተካሄደው ተግባራዊ ስልጠና ከዚህ በፊትም በተመሳሳይ ከከኦሮሚያ እና ከሲዳማ ክልሎች ለተውጣጡ ሰልጣኞች በአዳማና ሀዋሳ ከተሞች መሰጠቱ ይታወቃል ።

**የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት በአፍሪካ ነጻ የንግድ ቀጣና ስምምነት፣ በካፒታል ገበያ እና በሌሎች ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ለኢንተርፕራይይች ስልጠና ሰጠ።**

**ስልጠናው የተሰጠው በሲዳማ ክልል** ለሚገኙ አነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞችና ተቋማት (SMEs) አመራሮችና ባለሙያዎች ነው ።





በስልጠናው ላይ የተገኙት የሲዳማ ክልል የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ዋና ጸሐፊ አቶ ደመቀ ደፋሩ ስልጠናው የተቋማቱ አመራሮችና ባለሙያዎች በጉዳዩ ዙሪያ የተሻለ ግንዛቤ እንዲኖራቸው በማድረግ የላቀ ሚና እንደሚጫወት ተናግረዋል።



በ Africa continental free trade agreement (AfCFTA), Capital market, Association governance, business management and Promotional skill በሚሉ ርዕሶች የተሰጠው ስልጠና በሲዳማ ክልል የሚገኙ አነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይይች በአፍሪካ ገበያ ሊኖራቸው ስለሚገባው ሚና እንዲሁም በአመራር እና ፕሮሞሽን ዙሪያ ትልቅ ለውጥ እንደሚያመጣ ተጠቁሟል። ከጥቅምት 19-20/2017 ዓ/ም የተካሄደው ስልጠና የተሰጠው በኢትዮጵያ ንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክርቤት አስተባባሪነትና መሪነት እንዲሁም ከGIZ-SRVC በተገኘ የገንዘብ ድጋፍ ነው።

**የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ከGIZ SRVC ፕሮጀክት በተገኘ የገንዘብ ድጋፍ ከአማራ ክልል የተለያዩ ዞኖችና ወረዳች ለተውጣጡ ሰልጣኞች የአኩሪ አተር ምርትን እሴት በመጨመር የተለያዩ ምግቦችን ለማዘጋጀት የሚያስችል ስልጠና በግዮን ሆቴል ተሰጠ ።**

የስልጠናውን መጀመር አስመልክቶ የመግቢያ ንግግር ያደረጉት የአማራ ክልል ንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ዋና ጸኃፊ አቶ ንብረት ባንቲገኝ




የኢትዮጵያ ንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት የክልል ምክር ቤት አባላትን አቅም ለመገንባትና ተጨባጭ ለውጥ ለማምጣት በየጊዜው የሚሰጠውን ስልጠና አድንቀው እንደ ክልል ምክር ቤትም የተሻለ ንግድና ኢንቨስትመንት ለመፍጠር ጠንክረን እየሰራን ነው ብለዋል።





በመሆኑም የአባላትን አቅም ለመገንባትና ምርትና አገልገሎት ለማስተዋወቅ ሰፊ ስራ እየተሰራ መሆኑን ገልጸዋል ። አያይዘውም ይህ አይነት ስልጠና አሁን የምትሩትን ስራ በተሻለ መንገድ ተግባራዊ በማድረግ ቢዝነሳችሁንና ገቢያችሁን ለማሻሻል እድል ይፈጥራል ስለሆነም በትኩረት ስልጠናውን ተከታትላችሁ እንድታጠናቅቁ ሲሉ አሳስበዋል።

የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት የቢዝነስ ሊደርሽፕ አመራር አካዳሚ ኃላፊ የሆኑት አቶ ብስራት በለጠ በበኩላቸው ምክር ቤቱ ትኩረት አድርጎ ከሚሰራባቸውና ከተሰጠው ተልዕኮ የግሉን ዘርፍ መደገፍ መሆኑን ገልጸው በተለይም ንግድን ፣ኢንቨስትመንት ማስፋፋት፣ጥናትና ምርምር አድቮኬሲ እንዲሁም የአባላትን አቅም መገንባት መሆኑን ገልጸዋል።

ይህንን አይነት የተግባር ላይ ስልጠና ወስዶ ተግባራዊ ማድረግ ይገባል፣ ምክር ቤቱም የስልጠናውን ውጤታማነት ይከታተላል ተከታታይ የአቅም



ማጎልበቻ በተግባር የተደገፈ ስልጠና ይሰጣል፣ አፈጻጸም ይከታተልል ፣ ድጋፍ ከሚያደርጉ አጋር አካላትም የማሽነሪና ሌሎች ድጋፎች ለማድረግ ትስስር ይፈጠራል ብለዋል።

ስልጠናው ለሶስት ተከታታይ ቀናት የሚሰጥ ሲሆን የስልጠና አስተባባሪዎች ዶ/ር ቴወድሮስ ተስፋየ፣ ጎበዜ ጨቅሌን ጨምሮ ከ27 በላይ ተሳታፊዎች ተገኝተዋል።

የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅራት ምክር ቤት ከአባል የክልልና የከተማ የንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤቶች ለተወጣጡ ዋና








ጸሃፊዎች በአፍሪካ አህጉር ነፃ የንግድ ቀጣና(AfCFTA) በካፒታል ገበያ(Capital Market) እንዲሁም በአመራር ጥበብ( Leadership) ዙሪያ

ያዘጋጀው የሁለት ቀናት ስልጠና በኢሊሊ ኢንተርናሽናል ሆቴል ተካሂዷል።

**የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት፤ የመገናኛ ብዙሃን ለአገራዊ ኢኮኖሚ እንዲሁም ለግሉ ዘርፍ ልማት ባለው ሚና ላይ ያዘጋጀው ስልጠና በአዳማ ተካሄደ ።**

ስልጠናው ፤ ሰላም ለልማት ባለው ሚና፤ በአፍሪካ ነጻ የንግድ ቀጣና እና የዓለም አቀፉ ንግድ ድርጅት መርሆዎች፤ የሚድያ






ሚና በግሉ ዘርፍ እድገት እንዲሁም በምክር ቤቱ እየተተገበሩ ካሉ ፕሮጀክቶች መካከል GIZ/SRVC ድጋፍ እየተሰራ ስላለ እና በግብርና ላይ ትኩረቱን ባደረግ ፕሮጀክት ዙሪያ ነው የተሰጠው። ከመንግስትና ከግል ሚድያ የተወጣጡ ጋዜጠኞች ተሳትፈዋል።

በስልጠናዉ የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ዋና ጸሀፊ ዶክተር ቀነኒሳ ለሚ እና የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር የሚኒስትር ጽ/ቤት ሀላፊ ጂራታ ነመራ ተገኝተዋል።






**የኦሮሚያ የንግድና ዘርፍ ማህበራት ም/ቤት በጣሊያን ሀገር ኦክቶበር 9-12/2024 በተካሄደው የአለም አቀፍ የኮንስትራክሽን ኤክስፖ ላይ የሃገራችንን ልዑካን በመጋበዝ 17 በሴክተሩ ላይ ያሉ ነጋዴዎችን በኤግዝቢሽኑ ላይ እንዲሳተፉ አድርጓል።**



ይህ ኤግዝቢሽን በግንባታ ኮንስትራክሽን ዙሪያ ያሉ የሀገራችን ልዑካን ሰፊ ልምድ



ልውውጥ ያደረጉበት ባዛር መሆኑን ተሳታፊዎች ገልጸዋል።

**የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል የንግድና የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት በምክር ቤቱ ፕሬዚዳንት አቶ ቦጋለ ቢታኔ የተመራ ከ34 በላይ የንግድ ልዑክ ኢንዶኔዥያ ጃካርታ ከ October 9-12 በሚቆየው ትሬድ ኤክስፖ ላይ ተሳትፎ በሰላም ወደሀገር ቤት ተመልሷል።**



<u>ለደቡብ</u> ኢትዮጵያ ክልል ንግድ ስርአት ለውጥ የሚያመጣ ተግባር በይፋ ጀምረናል።ከዘልማድ ንግድ ስርአት ነጋዴው ወጥቶ ዓለም አቀፍ ገበያን እንዲቀላቀልና ዓለም የደረሰበትን ልክ እንዲመለከት የሚያስችል ተግባር ምክር ቤቱ በተቋቋመ ሁለት ወር ውስጥ በክልሉ የንግድና የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት አመቻችነት ተሰናድቶ በክልሉ የንግድና የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ፕሬዚዳንት(አቶ ቦጋለ ቢታኔ) መሪነት ከ34 በላይ የንግድ ልዑክ ኢንዶኔዥ ጃካርታ ይገኛል። ከልምድ ፈቀቅ አዲስ አሰራርንና ዝማኔን ጠበቅ!!



# የኢትዮጵያ ንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ገጽታ ከውጭ ሲታይ





ኢትዮጵያ ቻምበር
ETHIOPIA CHAMBER

# የግሉ ዘርፍ ድምጽ!

**ዋና አዘጋጅ ፡-**

ደበበ አበበ

**ከፍተኛ አዘጋጅ ፡-**

ስማቸው ተበጀ

**የፎቶግራፍ ባለሙያ፡-**

ያለምፍሬ በቀለ

FOLLOW US ON

www.ethiopianchamber.com

t.me/ethiopiachamber

facebook.com/EthiopianChamber

youtube.com/@ethiopianchamber

twitter.com/EthiopiaChamber

info@ethiopianchamber.com

+251115514005

**Ethiopian Chamber of Commerce & Sectoral Associations (ECCSA) Resource Center has stated giving service to member. The center is located at the head quarter of ECCSA.**

**It is a unit dedicated to serve the business community, its members and staffs with a range of timely and cost-effective information services which will enhance the decision-making process and competitiveness of the chamber system management and the business community.**

**It is also a WTO (World Trade Organization) Reference Center for the private sector, to enable business community to access online trade data and WTO-related documents on a continuous basis, to help identify market niches for the export of their products and services.**

**The center works on the principle of the 5Rs: providing the Right information to the Right person at the Right time in the Right quantity and Right quality.**

## The Center's Services

- ⇒ **Reference, Resources Loan & Interlibrary Loan Services**
- ⇒ **Internet & Electronic Resource Services**
- ⇒ **Support on information searching**
- ⇒ **Reprographic Service**
- ⇒ **Advising users on reference materials available in resource center.**
- ⇒ **Types of Materials in the Center**
- ⇒ **Books, Periodicals, Journals, Magazines**
- ⇒ **Audio and Video CD collections**
- ⇒ **E-Books & Publications**
- ⇒ **Business & Economic Statistics & Databases**
- ⇒ **Access to international organization's online information (WTO, ITC, UNCTAD, World Bank, PACCI, WCO, etc.)**

## For further information:

***Ethiopian Chamber of Commerce and Sectoral Associations ECCSA Resource & WTO Reference Center***

- ⇒ **Mexico Square, ECCSA Building**
- ⇒ **Ground Office , Room No. 13/14**
- ⇒ **Open to public Monday-Friday from 2:30 am to 5:00 pm**
- ⇒ **Tel: 251-115514005**
- ⇒ **Mob. 0966038499**
- ⇒ **Fax: 251-115517699**

